# እውነቱን ኣውጡ





አልገባኝም እኔ ምንድነው ምስጢሩ፤
የዘር ነው፤ ወይስ የፖለቲካ ችግሩ፤
የኢሕአድግ መርሐ ግብር ይመስክሩ፤
ከልማትና ሠላም፤ ውጭ ከተናገሩ፤
እኔ ምስክር ነኝ፤ እናንተም መስክሩ፤
ባንዳዎች ንገሩኝ ባንድላይ ተመካከሩ።



በሶሻሊዝም ስም፣ ያፈሰሳችሁት ደም፤
ዳግም ከጀላቹህ ያንን ለመድገም፤
ለደርግ፤ ኢሠፓ፤ እንዴት ሕግ የለም!?



ምንድነው ምስጢሩ፤ የናንተ ችግሩ፣
ኣልገባህ ብሎኛል፤ የናንተ ስሌት ቀመሩ፣
የዲሞክራሲ ጠላቶች ከጥንት ከጅምሩ፤
ለኔም ለናንተም ታሪክ ነው ምስክሩ።



የቅዱስ ያሬድ ትውልድ ቦታ የትግራይ መሬት፤
የግዕዝ ቋንቋ መፈጠሪያ የስልጣኔ ቀደምት፤
ኩራት ይሰማኛል መወለዴ ከዚች ቅድስት መሬት፤
እንዴት ሕዝባን ይላሉ ኣይደለም የኢትዮጵያ መሰረት!?



ለኢትዮጵያ ውድቀት፣ ድህነት፣ ሌተ ቀን የምታልሙ፤
እርዳታ አይሰጣት፤ እያላቹህ የምትቃወሙ፤
የእድገት ነቀርሣዎች ፊደል ያልቀሰሙ።


Africa BBC Graphic may 18, 2000

በሉ ነገም ሠልፍ ውጡ ሳታቋርጡ፤
ውጤት ከተገኘ ደግማቹህ ደጋግማቹህ ውጡ፤
መነኩሴ ቄስ ተብዬው መስቀላችን ያስቀምጡ፤
አጋንት ወርሰውታ ኣመሪካ፣ ኤውሮፓ፣ ሲርመጠመጡ።

የውጭ ጠላት ናቸው እንዳንል ቋንቋችን የምትናገሩ፤
የልማት፣ የሠላም፣ ጋሬጣችን የሻዓብያ ደቀመዝሙሩ፤
ደህና ኣልባሳት ለብሳቹህ ለኢሳያስ ቅዳሴ ዘምሩ፤
የዘመኑ ጣዖታቹህ እሱ ነው ምፅዋት ገብሩ።



በአርበኞች፣ እርዳታ ስም ገንዘብ ለኤርትራ!

በኤርትራ ቲቪ እንድትታዩ ስትቅበጠበጡ፤
አርበኞች ተብላችህ እንድትመረጡ፤
ቅድሚያ £500 ፓውንድ ለአርበኞች አዋጡ፤
ገንዘቡን በኢሳያስ ስም ባንክ አስቀምጡ፤
ይህ ነው ሥራቹህ ሌላ ካላቹህ እውነቱን አውጡ።

ኣሉላ ዮሓንስ alula2005@lycos.com
መጋቢት 1998 ሎንደን